## ❖ የማንነት ፖለቲካ ... የልሂቁ ሚና

... የአፄ ምኒልክ ግዛታዊ መስፋፋት ይዞት የመጣው አንድ ውጤት በማህበረሰብ ደረጃ ሀገራዊ ውህደትና አንድነት የማጠናከር ፈተና ነው (ማርካኪስ፣ ባህሩ ዘውዴ፣ ክላፓም፣ ሣራ ቮን)። የየወቅቱ የኢትዮጵያ ልሂቃንም ይህን እውን ማድረጊያ ያሏቸው ዘዴዎችና መፍትሄዎች ጠቁመዋል። ሊተገብሩም ሞክረዋል። ከጉዳዩ በወቅቱ ልሂቃን እንዲህ መነሳት እና በጭብጥነት ከቀረቡ ሀቆች ይዘት ብቻ የተጠቀሰውን የማንነት ፖለቲካ ታሪካዊነት ማየት ይቻላል። ማን ወዴትና ምን ስለሆነ ''የውህደቱ'' ዓላማ ወይም ግብዓት ሆነ... ? ...

------------------------------ /// ------------------------------

... በዛ ያሉት የዘመኑ ማህበረሰቦች የተሰነዘረባቸውን የምኒልክ ሰራዊት ጥቃት አጠቃላይ መጥፊያ ብለው በማመን ወይም ከልማድ በተያያዘ ጀብደኝነት ተጋፍጠው ከመጥፋት ይልቅ እጅ በመስጠት ወይም በውጊያው ሳይገፉ በማቆም ገብረዋል። የዚህ አንድ ዋነኛ ምክንያትም ህልውናችን በተሻለ ይቀጥላል የሚል ተስፋ ነበር። የተጠቀሰው ብሔረተኛ አርበኝነት ግልባጭ እውነትም ይህንን አያይዞ የዳጠ መሆኑ ነው። አቶ አንዳርጋቸው እንደሚሉት *''...የራሳቸውን ብሔረተኝነት ለማዳበር የማህበራዊም ይሁን የኢኮኖሚ መሰረት ያልነበራቸው...የርስ በርስ የመጠፋፋት ወይም በነጮች የባርነት ቀንበር ስር የመውደቅ አስፈሪ አደጋ ...''* የተጋረጠባቸው ባላባትና የእነዚህ ማህበረሰቦች መሳፍንት አዲስ የተፈጠረውን ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ''መቀበል የሚቸግራቸው'' አልነበሩም። ይህ መሆኑም የተጠቀሰው የግልባጭ ግምት ቢያንስ ምናባዊ ልጠጣ እንዳልሆነ ይጠቁማል። በተጨማሪም ከዛ በላይ በሆነው የሰው ልጅ ደመነፍሳዊ ስሜትም የሚደገፍ ነው። በመስፋፋቱ የተካተቱት ማህበረሰቦች ከአድዋ ድል በኋላ በተለይ የተነፈጉት በፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር የሚገለፅ ይህን መሰል ቁርኝትና ተጠቃሚነት ነበር። ...

------------------------------ /// ------------------------------

... ማንነት (ብሔርን ጨምሮ) የጋራ መስተጋብር፣ ከዚህም በመነጨ የሚጋሩት ግንዛቤ (ተጣጣሚ ሆኖም ሳይሆንም የታመነበት) በየጊዜው የሚገነባ ክፍት፣ ተለጣጭ እና ተለዋዋጭ መገለጫዎች ሊኖሩት የሚችል ማህበራዊ እውነታ ውጤት ነው። ሌላ አንድ መሰል ፍጡር በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው በግል ትርጉም የሚሰጥ ቋንቋ ሊኖር እንደማይችል ሁሉ የዚያኑም ያህል በአንድ ደሴት ተነጥሎ የተኮተኮተ ''አንድ ግለሰብ የብሔር ማንነት የለውም''። ይህ ትርጉም የለሽና በእውነታ የሌለ ነው። በዋናነት የብሔር ማንነት ማህበራዊ ምደባ ነው። እንደ ማህበረሰባዊ ጭብጥና ፅንሰ ሀሳብም ከዚህ ውጪ የሆነ ትርጓሜም ሆነ ይዘት የለውም። ...

------------------------------ /// ------------------------------

... *''የለውጥ ፈር ቀዳጆች''* በሚል ስለ ኢትዮጵያ ልሂቅ፣ በተለይ ደግሞ የማከል ለውጥ አቀንቃኝ ስለሆኑት ቀደምት ልሂቃን ጠቃሚ ሥራ ያበረከቱልን ባህሩ ዘውዴ፤ ስለ ታሪክ ያለንን ዕይታ በአንድ መሥመር ያስቀምጡታል። *''እንደ ኢትዮጵያውያን ታሪክ እጅግ የተጠናወተው (ኦፕሴሽን) ጥቂት ህዝብ ብቻ ነው''* (ፓዮኔርስ ኦፍ ቼንጅ ኢን ኢትዮጵያ፣ 141)። ገብሩ ታረቀ ደግሞ እንደሚከተለው ይገልጹታል። *''እንደ ኢትዮጵያ ደርዝ ያለው ባለታሪክም፣ በዚህ ታሪኩም የጎበጠ ሀገር በአፍሪካ ብዙ የለም።'' (ኢትዮጵያ ፓወር ኤንድ ፕሮቴስት፣ xii)።* ... ይህ በገሃድ ከሚገለፅባቸው ጉዳዮች መካከል ዋናው ከኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ጋር የተያያዘው እና ለዚሁ ሂደት አዲስ ምዕራፍ ከፍቶ የቀጠለው የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ያነሳው የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ነው። የዘመናዊት ኢትዮጵያ አፄያዊ መንግሥት ከጥንታዊቷ አቢሲኒያ ያለው ቀጣይነትና ልዩነት፣ ህብረብሔራዊነትና ውህደት፣ ወጥ ግዛታዊ አንድነትና የብሔሮች መብት ላይ የቆመ ፌዴራላዊ አንድነት ወዘተ. በዚህ ሥር ተካተው የሚቀርቡ አወዛጋቢ ጭብጦች ሆነው እናገኛለን። የታሪክ ደርዛችንን ጥልቀት ብሎም አጉባጭ ክብደት በተጨባጭ የሚያሳይ አስረጂ በመሆንም ቀጥሏል። ...